# ዳሩ ሲደፈር መሃሉ ዳር ይሆናል!!
## በእናቶችና በአባቶች ደምና አጥንት ተከብሮ የቆየው
## የአገር ሉዓላዊነታችን በገፀ በረከትነት ሲቀርብ በቸልታ አናየውም!!

ኢትዮጵያዊነት ተነግሮ የማያልቅ መንፈሳዊ ቅርስ፣ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ነው:: የዘርና የሃይማኖት ልዩነቶች የተዋሃደባት፤ በብሄር ብሄረሰቦቿ የተለያዩ ባህል ውህደት ህብር ውበት የፈሰሰባት የነፃነት ምድር ነች:: ኢትዮጵያዊነት የረጅም ጊዜ የታሪክ አስኳል ገድል፣ እናቶችና አባቶች ደማቸው ተቀላቅሎ የፈሰሰባት፣ አጥንታቸው ተነባብሮ የወደቀበት የአርበኞች አገር ናት:: በባርነት ቀንበር ስር ተይዘው ለነበሩ የዓለም ጭቁን ህዝቦች በተለይም ለአፍሪካ ህዝብ በነፃነት ፋና ወጊነት ስትታወስ የኖረች የቃል ኪዳን ሀገር ናት::

አዎ!ይህች ምድር ጀግኖች እንዳሏት ባንዳዎችም አሏት:: እምቢ ለነፃነቴ ያለው ቴዎድሮስ ተፈጥሮአዊ ሞትን የሚያሸንፍበት የዕምነት ኃይል ያገኘበት የእናት አገሩ ፍቅር ነው ሕይወቱ ላይ እንዲወስን ያደረገው:: « ክንዴን አንድ ጊዜ አሳያቸዋለሁ፤ እንደገና ከመጡም እደግማቸዋለሁ:: የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው::» ያለው አሉላ አባነጋም የአብራኩ ክፍዮች የሆኑት የዛሬው ገዢዎች በቂምና በበቀል የታወሩት ወያኔ (ኢሕአዴግ) ኤርትራን ከእናት ሀገር እንድትገነጠል ትልቁን ሚና በመጫወት ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ሀገር እንድትሆን በማድረግ በወደቡ ላይ የነበራትን ትልቅ የኤኮኖሚ ጥቅም እንድታጣ አድርጏታል::

በሱማሌ ግዛት ውስጥ ጣልቃ በመግባት በሰፊው የሶማሌ ሕዝብና በእኛ መካከል ለትውልድ የሚተላለፍ የጠላትነት መንፈስ እንዲፈጠር ትልቁን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል:: በመላው የእስልምና ተከታይ አገራትም በመጥፎ ዓይን እንድንታይ አድርጏል:: ለረጅም ዘመናትም በፍቅርና በመተሳሰብ ሲኖሩ የነበሩ የተለያዩ ጐሳዎች አባል የሆኑ ዜጐቻችን እርስ በእርስ እንዲጋጩ በማድረግ ለረዥም ጊዜ በስልጣን የሚቆይበትን ስልት በሕዝብ ዕልቂት በመንደፍ ላይ ይገኛል::

ዛሬም ይህ እኩይ ተግባሩ እንደቀጠለ ነው:: በቅርቡም በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እንደተገለፀው በምእራብ ኢትዮጵያ ድንበር የሚገኘውን የኢትዮጵያን ግዛት ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቷል:: ከ28 በላይ ኢትዮጵያዊያን ተይዘው በሱዳን በእስር ላይ ይገኛሉ:: ቤቶች ተቃጥለዋል፣ነዋሪዎች ተፈናቅለዋል ይሄ ድርጊትም በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን አስቆጥቷል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞም ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ በፓርላማ ባደረጉት ንግግር « ኢትዮጵያዊያኖች የማያርሱትን መሬት ለሱዳን ገበሬዎችና ባለሃብቶች እንዲሰጥ ተደርጏል::» በማለት አረጋግጠውልናል::

ይሄ ድርጊታቸውም ከምንም በላይ እኛ ኢትዮጵያዊያንን አስቆጥቶናል፣ አስቆጭቶናል:: ይህም በመሆኑ በአሜሪካ፣በአውሮፓና ካናዳ እንዲሁም በሌሎች ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት የዓለም ክፍል ተቃውሞች እንደቀጠሉ ነው::

ከዚህም ጋር ተያይዞ በለንደን የኢትዮጵያዊያን ሲቪክ ኮንሶርቲየም (Ethiopian Civic Consortium) ይህንን ተቃውሞና ሰልፍ በመደገፍና ከሌሎች አጋር ድርጅቶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ጋር በመሆን በጋራ ይታገላል:: በዚህም መሰረት ለለንደንና አካባቢው ለሚገኙ ነዋሪዎች እሁድ (1 June 2008) ሕዝባዊ ስብሰባ አዘጋጅቷል:: በስብሰባው ተሳታፊዎችና አስተባባሪዎች አዲስ ግብረ ሃይል በማቋቋም የኢትዮጵያን ግዛት ለማስመለስና የታሰሩት ዜጐቻችን እንዲፈቱ ለማድረግ በሚደረገው ሁለገብ የትግል እንቅስቃሴ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አባላት ጋር በመሆኑ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ዝግጅቱን ይገልጻል::

*«ታሪካችን በማረሻ ብዕር፣ ባልተገረዘ አንደበት እየተዘለፈ ነው:: የኢትዮጵያ ጀግኖች በሙታን ዓለም ዳግመኛ እየተገደሉ ፤ ያሉትም እየተወገሩ ነው:: አላወቁም እንጂ ጀግና ገዳይ የለውም ፤ ዘላለማዊ ነው፣ ሕያው ነው:: ጀግና ይወለዳል እንጂ አይሞትም፣» ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን*

ኢትዮጵያ አንድነቷ ፀንቶ፣ ሉዓላዊነቷ ተከብሮ ለዘለዓለም ትኑር!!
(Ethiopian Civic Consortium & Concerned Ethiopian in UK)